በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የተሻሻለው የግ/ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ስርዓት

ማስፈፀሚያ ደንብ ቁጥር 159/2010 ዓ.ም

ላይ ከፍትህ አካላትና ፈጻሚ አካላት ጋር የጋራ ግንዛቤ ለመያዝ

የተዘጋጀ የመወያያ ጽሁፍ

አቅራቢ፡-

አዲሱ ሞላ

መጋቢት 2010 ዓ.ም

ባህር ዳር

ይዘት

- መግቢያ
- ክፍል አንድ
  - ጠቅላላ
  - ትርጓሜ
  - ዓላማዎች
- ክፍል ሁለት
  - የግጠር መሬት ስለማግኘት፣ ስለመጠቀምና ስለማስተዳደር
- ክፍል ሶስት
  - ስለገጠር መሬት አጠቃቀም እቅድ ዝግጅት፣ አተገባበርና ቁጥጥር
- ክፍል አራት
  - የገጠር መሬትን ስለመለካት፣ ስለመመዝገብና የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ስለመስጠት
- ክፍል አምስት
  - ስለገጠር መሬት ምዝገባ መረጃ አያያዝ፣ ወቅታዊ አደራረግና ስለአገልግሎት ክፍያዎች

የቀጠለ...

- ክፍል ስድስት
  - ስለደንቡ አስፈጻሚ አካላት
- ክፍል ሰባት
  - ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

መግቢያ

- የክልሉ ህግ አውጪ ምክር ቤት ፡
- የተሻሻለውን የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 ዓ.ም ያወጣና ዝርዝር ጉዳዮች በደንብ እንደሚደነግጉና
- የአዋጁን ሙሉ ተፈጻሚነት የሚያሳልጡ ድንጋጌዎችን ማዉጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤
- በህግ ተርጓሚ እና ፈጻሚ አካላት መካከል የጋራ ግንዛቤ መፍጠር ለፍትህና መልካም አስተዳደር መስፈን ወሳኝ ጉዳይ በመሆኑ በተሻሻለው ደንብ ላይ ውይይት ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ይህ የመወያያ ጽሁፍ ተዘጋጅቷል።

የቀጠለ....

- የአማራ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት:-
  - በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 እና
- ተሻሽሎ በወጣው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 252/2009 ዓ.ም አንቀጽ 60 ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌዎች ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

አጭር ርዕስ (አንቀጽ 1)

- ይህ “ደንብ” የተሻሻለው የግጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ማስፈፀሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 159 / 2010 ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

የቀጠለ...

ትርጓሜ (አንቀጽ -2)

- የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-
- “አዋጅ” ማለት የተሻሻለው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009ዓ.ም ነው።
- “ባለሀብት” ማለት የኢንቨስትመንት ፈቃድ አውጥቶ ግብርናውን ከኢንዱስትሪው ጋር በማስተሳሰር ዘርፉን ወደላቀ ደረጃ የሚያሸጋግርና የፕሮጀክት እቅድ በመንደፍ መዋእለ-ንዋዩን በገጠር መሬት ላይ እያፈሰሰ ለኢኮኖሚው እድገት የራሱን አስተዋፅኦ የሚያበረክት ማንኛውም ሰው ነው።

የቀጠለ...

- "የኢንቨስትመንት መሬት" ማለት የኢንቨስትመንት ፈቃድ በተሰጠው ግለሰብ፣ ቡድን ወይም ድርጅት ስም ተመዝግቦ ለተወሰነ ጊዜ የመጠቀም መብት የተገኘበት የግጠር መሬት ነው።
- "ገማች ኮሚቴ" ማለት በገጠር መሬት ይዞታ ላይ የለማን ንብረትና የመፈናቀያ ካሳ መጠን ለመተመን ልዩ እውቀት ወይም ልምድ ወይም ሁለቱም ያሉት ሆኖ በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ውስጥ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የክልሉ መንግሥት ተቋማት ተወጣጥቶ የሚሰየም የባለሙያዎች ስብስብ ነው።

የቀጠለ...

- “በመሬት ላይ የለማ ንብረት“ ማለት በይዞታ መሬት ላይ የለማ ማናቸውም ንብረት ሲሆን፣ ተረፈ ምርትንና የመሬቱን ለምነት ለማሻሻል ታስበው የተከናወኑ ስራዎችን ጭምር ያጠቃልላል።
- “ቀመር” ማለት የመሬት ይዞታውን ወይም የመጠቀም መብቱን እንዲለቅ ለሚወሰንበት ባለይዞታ የሚከፈለውን ካሳ ወጥ በሆነ መንገድ ለመገመት የሚያስችል ስሌት የሚከናወንበት የአሰራር መሳሪያ ነው።

የቀጠለ...

- “የመሬት ሀብትና የለማ ንብረት ቆጠራና ምዝገባ” ማለት በማናቸውም የአስተዳደር ወሰን የሚገኝን ህጋዊ የገጠር መሬት ይዞታ በመጠን፣ በአገልግሎት አይነትና በይዞታዉ ላይ የለማ ንብረት ለይቶ የመመዝገብና መረጃውን አደራጅቶ የመያዝ ተግባር ነው።
- “የመሬት አያያዝ” ማለት የገጠር መሬት ለተለያዩ ጥቅሞች እንዲውል በሚደረግበት ጊዜ ዘላቂ ጥቅም መስጠት ይቻለው ዘንድ የሚደረግ እንክብካቤ ነው።

የቀጠለ...

- “የመሬት ግምገማ” ማለት ስነሂወታዊና አካላዊ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ ዘላቂ ጥቅም የሚሰጠውን የመሬት አጠቃቀም አማራጭና አያያዙን ለመወሰን የሚረዳ ስልት ነው።
- “የመሬት የማምረት አቅም ደረጃ” ማለት መሬት በአካላዊ መረጃዎች መሰረት ተገምግሞ ከዘላቂ ጥቅም አንፃር የሚኖረው የማምረት ችሎታ ነው።

የቀጠለ...

- “የመሬት የተስማሚነት ደረጃ” ማለት በመሬት አጠቃቀም ጥናትና አሰሳ ወቅት አንድ መሬት አካላዊና ምጣኔ-ሃብታዊ በሆነ ጥናትና ትንተና ለተለየ ወይም ለታወቀ የልማት አገልግሎት አማራጭ ያለው የተስማሚነት ደረጃ ነው።
- “የቀበሌ መሬት አጠቃቀምና አያያዝ ዕቅድ” ማለት በገጠር ቀበሌ በማሳ ደረጃ የተሻለ ጥቅም እንዲሰጥ ታስቦ የሚዘጋጅ የመሬት አጠቃቀምና አያያዝ ዕቅድ ነው።

የቀጠለ...

- “አሳታፊ የቀበሌ መሬት አጠቃቀምና አያያዝ እቅድ” ማለት በቀበሌው ክልል ውስጥ መሬት በስነ-ህይወታዊና አካላዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በማህበራዊ መረጃዎች መሰረት አጠቃቀሙ በህብረተሰቡ ተሳትፎ የሚወሰንበት እቅድ ሲሆን መላ ዝግጅትና አካሄዱን ያጠቃልላል።
- “የግጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ” ማለት በቀበሌው ነዋሪ ህዝብ የተመረጠ ሆኖ በቀበሌም ሆነ በንኡስ ቀበሌ ደረጃ የተቋቋመ ኮሚቴ ሲሆን፣ በአዋጁ መሰረት የቀበሌውን መሬት ለማስተዳደር ስልጣን የተሠጠው አካል ነው።

የቀጠለ...

- “ማጨሻ” ወይም (የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ) ማለት ማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ በይዞታ መሬቱ ላይ የመኖሪያ ቤት ሰርቶ በርግጥ እየኖረበት ያለ ቦታ ነው።
- አንድ ሄክታር መሬት ማለት እንደየአካባቢው አጠራር ጠቅላላ ስፋቱ በአራት ቃዳ ወይም አራት ጥማድ ወይም በሌላ በማናቸውም አቻ መለኪያ የተወሰነ መሬት ነው።

የቀጠለ...

በአዋጁ አንቀጽ 2 ከንኡስ አንቀፅ 1 እስከንኡስ አንቀጽ 47 የተዘረዘሩትና በዚህ ደንብ ውስጥ በተለያዩ ስፍራዎች ጥቅም ላይ የዋሉት ቃላትና ሀረጎች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጓሜ እንደያዙ ይቀጥላሉ።

- ደንቡ ከዚህ በታች የተመለከቱት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-
  - በአዋጁ ውስጥ የተዘረዘሩት የግጠር መሬት ባለይዞታዎችና ተጠቃሚዎች የተለያዩ መብቶችና ግዴታዎች በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግና፤
  - የክልሉ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ቢሮም ሆነ የተዋረድ አካላቱ ኃላፊነታቸዉን በአግባቡ እንዲወጡ በማድረግ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ስርዓቱ የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እንዲያስችል ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር።

የግጠር መሬት ስለማግኘት (አንቀጽ - 4)

- ዕድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ፣ በክልሉ ውስጥ የሚኖርና በግብርና ስራ ለመተዳደር የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የግጠር መሬት ይዞታ በነፃ የማግኘት መብት አለው።

የቀጠለ...

- በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ስር የተደነገገው ቢኖርም በመሬት ባንክ በትርፍነት ተመዝግቦ የተያዘው የግጠር መሬት ለሁሉም መሬት ጠያቂዎች የማይዳረስ ሆኖ ሲገኝ በግብርና ስራ መተዳደር ለሚፈልጉና
- ወላጆቻቸውን በሞት ላጡ ህጻናት፣
- አካል ጉዳተኞች፣
- አቅመ-ደካሞች፣
- ሴቶችና
- አረጋውያን እንደቅደም-ተከተላቸው ቅድሚያ ይሰጣቸዋል።

የቀጠለ...

- በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ስር የተጠቀሱት ወገኖች በሌሉበት ጊዜ ወይም ቅድሚያ አግኝተው ከተስተናገዱ በኋላ ትርፍ መሬት መኖሩ የታወቀ እንደሆነ ይኸው መሬት በህዝብ ተሳትፎ ለሚለዩ ሌሎች አመልካቾች ከዚህ በታች በተገለፀው ቅደም-ተከተል እንዲሰጣቸው ይደረጋል፡-
  - ጎጆ የወጣና ልጅ ያለው፤
  - ጎጆ የወጣና ልጅ የሌለው፤
  - ያላገባ ወይም ጎጆ ያልወጣ ወጣት፤
  - ያገባ ሆኖ በትዳር ጓደኛው ስም የተመዘገበ የጋራ ይዞታ ቢኖረውም የራሱ ይዞታ የሌለው፤
  - በህግ ከተፈቀደው አነስተኛ የመሬት ይዞታ በታች መሬት ያላቸው ባለይዞታዎች።

የቀጠለ...

- ስራቸውን በክልሉ ውስጥ የሚያካሂዱ ፡
  - መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣
  - የሃይማኖት ተቋማትና የብዙሃን ማህበራት ለገንዘብ ትርፍ እስካላዋሉት ድረስ የአርሶ-አደሮችን በመሬት የመጠቀም መብት በማይፃረር አኳኋን ተግባራቸውን የሚያከናውኑበት የገጠር መሬት በይዞታ የማግኘት መብት ይኖራቸዋል።
- እነዚህ አካላት አዋጁ ከመውጣቱ በፊት የነበራቸው የይዞታ መጠን የተጠበቀ ቢሆንም ወደፊት ለሚያካሂዷቸው አዳዲስ ግንባታዎች ሊሰጥ የሚችለው የመሬት ይዞታ መጠን ይህንን ደንብ ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል።

የቀጠለ...

በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2)ና (3) ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጉዳዩ በሚመለከተው አካል በኩል ተደራጅተው ለሚቀርቡ ወጣቶች የሚሰጥ ትርፍ የገጠር መሬት የተገኘ እንደሆነ እንደአግባብነቱ ለግብርናም ሆነ ከግብርና ውጭ ለሆኑ ተግባራት ይጠቀሙበት ዘንድ ይኸው መሬት በጊዜያዊ ውል እንዲሰጣቸው ሊደረግ ይችላል። ዝርዝር አፈጻጸሙ በመመሪያ ይወሰናል።

ዝቅተኛው የመሬት ይዞታ መጠንና ከፍተኛው ጣሪያ የተወሰነ ስለመሆኑ (አንቀጽ- 5)

- በክልሉ ውስጥ የገጠር መሬት ባለይዞታዎች የሚይዙት ዝቅተኛው የይዞታ መጠን፡
  - በዝናብ የሚለማ ሲሆን ከ0.25ሄ/ር፣
  - በመስኖ የሚለማ ሲሆን ከ0.06 ሄክታርና
  - ለመኖሪያ ቤት መስሪያ ሲሆን ደግሞ ከ0.02 ሄክታር ሊያንስ አይችልም።
- በማናቸዉም ሁኔታ ቢሆን በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ስር ከተደነገገው መጠን በታች ማሳን መከፋፈል አይቻልም።
- ከፍተኛው የመሬት ይዞታ መጠን ፡
  - በደጋና በወይና ደጋ ሲሆን ከ7 ሄክታርና
  - በቆላ አካባቢዎች ደግሞ ከ10 ሄክታር የበለጠ ሊሆን አይችልም።

ስለገጠር መሬት ሽግሽግ(አንቀጽ- 6)

- ይህ ደንብ ከሚፀናበት ቀን ጀምሮ በክልሉ ውስጥ በየትኛውም የገጠር አካባቢ የመሬት ሽግሽግም ሆነ ክፍፍል አይካሄድም።
- በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር የሰፈረው ድንጋጌ በመስኖ የሚለማን መሬት ለተለያዩ ተጠቃሚዎች በሽግሽግ የማከፋፈልን ተግባር የሚከለክል አይሆንም።
- ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (1) ስር የሰፈረው ድንጋጌ ቢኖርም በመንግሥት ወይም መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ድጋፍ በተገነቡ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ምክንያት መሬታቸውን ያጡ ባለይዞታዎች በመስኖ ተጠቃሚ ከሆኑ ሌሎች ወገኖች መሬት በክፍፍል እንዲያገኙ ይደረጋል። ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።

የቀጠለ...

- በዘመናዊ መስኖ ከሚለማ መሬት ላይ ለመስኖ መሠረተ-ልማት አውታሮች ግንባታና መሰል አገልግሎቶች፣ እንዲሁም የተበታተኑ ይዞታዎችን በተቻለ መጠን ወደ አንድ አካባቢ ለማሰባሰብና ለመስኖ ውሃ አጠቃቀም አመችነት ሲባል ይዞታቸውን ያጡ ባለይዞታዎችን ጥቅም በሚያስከብር መንገድ ሽግሽግ በልዩ ሁኔታ ሊካሄድ ይችላል።
- በዘመናዊ የመስኖ መሠረተ-ልማት አውታሮች ግንባታ ምክንያት መሬታቸው የተወሰደባቸው ባለይዞታዎች በመስኖ ከሚለማው መሬት ውስጥ እንደሁኔታው እየታየ በሽግሽግ እንዲያገኙ ሊደረግ ይችላል።

የቀጠለ...

- የመስኖ መሬት ሽግሽግ አግባብ ባለው ወረዳ አስተዳደር የቅርብ ድጋፍና ክትትል በወረዳው የግጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት እየታገዘ የመስኖ ልማት ተጠቃሚዎች በሚመርጧቸው የኮሚቴ አባላት አማካኝነት ይካሄዳል፤ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡
- የመስኖ መሬት ሽግሽግ በሚካሄድበት ጊዜ ቋሚ ሰብል ያለበት መሬት የደረሰው ማንኛውም አርሶ-አደር ለቀድሞው ባለይዞታ ተገቢውን ካሣ በቅድሚያ መክፈል ይኖርበታል።

የቀጠለ....

- በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (7) ስር የተደነገገው ቢኖርም መሬቱ የደረሰው ባለይዞታ ካሣውን በአንድ ጊዜና በቅድሚያ የመክፈል አቅም የሌለው ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የካሣ ክፍያውን የክልሉ መንግሥት ቅድሚያ ከከፈለ በኋላ የከፈለውን መጠን ከባለግዴታው የመሰብሰብ መብት ይኖረዋል። ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።
- የመስኖ መሬት ክፍፍል በሚካሄድበት ጊዜ የመሬት ይዞታ ያላቸው ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ፡
- ወላጆቻቸዉን በሞት ያጡ ህፃናት፣
- አካል ጉዳተኞች፣
- አቅመ-ደካሞች፣
- ሴቶችና
- አረጋውያን ቅድሚያ ይሰጣቸዋል።

ስለ ገጠር መሬት ኪራይ (አንቀጽ -7)

- በአዋጁ አንቀጽ 15 ንኡስ አንቀጽ (8) ስር በተደነገገው መሰረት ማናቸውም የገጠር መሬት ኪራይ ውል:-
- እስከ ሁለት አመት ለሚዘልቅ ጊዜ የተደረገ ከሆነ መሬቱ በሚገኝበት የቀበሌ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት
- ከዚህ ለበለጠ ጊዜ የተደረገ ከሆነ ደግሞ መሬቱ ለሚገኝበት ወረዳ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት ቀርቦ መመዝገብ ይኖርበታል።

የቀጠለ...

- የውሉ ስምምነት በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች የሚወሰን ሆኖ የሰነዱን አዘገጃጀትና ይዘት አስመልክቶ ሙያዊ ድጋፍና ምክር አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ይኸው እንደሁኔታው በወረዳው ወይም በቀበሌው ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት አማካኝነት ሊሰጣቸው ይችላል።
- የትኛውም የመሬት ኪራይ ክፍያ ከመሬቱ በሚገኝ ሰብል፣ በየምርት ወቅቱ ለባለይዞታው በሚሰጥ አበል ወይም በአንድ ጊዜ ወይም በየዓመቱ ተቆርጦ በሚሰጥ የእህል ወይም የጥሬ ገንዘብ መጠን ሊፈፀም ይችላል።
- በጽሁፍ ያልተደረገና ጉዳዩ ወደሚመለከተው አካል ቀርቦ በወቅቱ ያልተመዘገበ የገጠር መሬት ኪራይ ውል ስምምነት ከነጭራሹ እንደሌለ ይቆጠራል።

የቀጠለ...

- የመሬት ኪራይ ውል አግባብ ላለው ጽህፈት ቤት ቀርቦ በሚመዘገብበት ወቅት ለዚሁ የተወሰነው የአገልግሎት ክፍያ ይፈጸማል፤ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።
- በአዋጁ አንቀጽ 15 ንኡስ አንቀጽ (10) ስር በተደነገገው መሰረት የኪራይ ውሉን እንደገና ለማደስ የሚፈልግ ወገን የኪራይ ዘመኑ ሊያበቃ አንድ ዓመት ሲቀረው ውሉን ለማደስ እንደሚፈልግ ጠቅሶ ለሌላኛው ተዋዋይ ወገን በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት።

የቀጠለ...

- 7. ማናቸውም የግጠር መሬት ኪራይ ውል ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ተፈፃሚነቱ አከራዩን ብቻ ሣይሆን ወራሾቹንም ሆነ በመሬቱ ላይ መብት ያላቸውን ሌሎች ወገኖች ጭምር የሚያስገድድ ይሆናል።
- 8. ተከራይ መሬቱን በአግባቡ ካለመያዙ የተነሣ አከራይ በሚመለከተው የመንግሥት አካል አማካኝነት የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው ወይም አስተዳደራዊ እርምጃ የተወሰደበት እንደሆነ አከራይ በውሉ የተወሰነው የጊዜ ገደብ ከማብቃቱ በፊት የኪራይ ውሉን እንዲያፈርስ በቂ ምክንያት ሊሆነው ይችላል።

የገጠር መሬት ይዞታን ከግል ባለሃብት ጋር በጋራ ስለማልማት (አንቀጽ -8)

- ማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ በመሬት የመጠቀም መብቱን በሚመለከት ከግል ባለኃብት ጋር በሚያደርገው ውል መሰረት በጋራ ሊያለማ ይችላል፡-

- ባለሃብቱ የሚጠቀምበት አዲስ ቴክኖሎጂ የአካባቢውን ህብረተ-ሰብ ሕይወት ለመቀየር ጠቀሜታ ያለውና አርሶ-አደሮች ከአሠራሩ እንዲማሩ እድል የሚሰጥ ከሆነ፤

የቀጠለ....

- የተመረተውን ምርት ከአርሶ-አደሮች ጋር አስቀድሞ በሚደረግ ስምምነት መሰረት ለመረከብ ወይም ለማቀነባበር የሚችል ከሆነ፤
- በአንድ አካባቢ የሚገኙ አርሶ-አደሮችን ሳያፈናቅል ተጠቃሚ የሚያደርጋቸው ሆኖ ከተገኘ፤
- በተቻለ መጠን በቅድሚያ ለሀገር ውስጥ ምርት በስፋት ማቅረብን መሰረት አድርጎ ከሃገር ውስጥ ፍጆታ በላይ ትርፍ ምርት በሚኖርበት ጊዜ ደግሞ ለዉጭ ሃገር ገበያ ጭምር ማቅረብ የሚችል ከሆነ።

የቀጠለ...

- አርሶ-አደሩና የግል ባለሀብቱ የሚያደርጉትን ስምምነት የያዘው ሰነድ በአዋጁ አንቀጽ 18 ንኡስ አንቀጽ (2) መሰረት አግባብ ላለው የወረዳ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት ቀርቦ መመዝገብ አለበት።
- የስምምነት ሰነዱ አጠቃላይ ይዘት ይህንን ደንብ ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል።

በግጠር መሬት ይዞታ የመጠቀም መብትን በብድር ዋስትና ስለማስያዝ (አንቀጽ -9)

- ማንኛውም የግጠር መሬት ባለይዞታ ከ30 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ በመሬቱ የመጠቀም መብቱን የብድር አገልግሎት እንዲሰጥ ለተፈቀደለት ህጋዊ የፋይናንስ ተቋም የብድር ዋስትና አድርጎ ማስያዝ ይችላል።
- ባለይዞታው በመሬቱ የመጠቀም መብቱን የብድር ዋስትና አድርጎ ለማስያዝ ማሳው የሁለተኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተርና ካርታ እንዲኖረው ያስፈልጋል።
- ማናቸውም የብድር ውል ስምምነት ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ተፈፃሚነቱ ተበዳሪውን ብቻ ሣይሆን ወራሾቹንም ሆነ በመሬቱ ላይ የመጠቀም መብት ያላቸውን ሌሎች ወገኖች ጭምር የሚያስገድድ ይሆናል።

የቀጠለ...

- ተበዳሪው በብድር ውሉ ውስጥ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ እዳውን ያልከፈለ እንደሆነ አበዳሪው በብድር ውሉ ለተጠቀሰው ጊዜ በመሬቱ የመጠቀም መብት የሚኖረው ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የዚሁ መብቱ ወሰን በመሬቱ ላይ ከተሰጠው **የመጠቀም መብት** ያለፈ ሊሆን አይችልም።
- በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) ስር የተደነገገው ቢኖርም **አበዳሪው መሬቱን በማከራየት ወይም ራሱ በማልማት በውሉ ውስጥ ከተጠቀሰው ጊዜ በፊት ቀሪውን እዳ ማግኘት ከቻለ** በውሉ ከተጠቀሰው ጊዜ በፊት በመሬቱ የመጠቀም መብቱ ይቋረጣል።

ይዞታን ስለመለዋወጥና ኩታ-ገጠም ስለማድረግ(አንቀጽ-10)

- ማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ ማሳዎችን ለማቀራረብም ሆነ ኩታ-ገጠም ለማድረግ ሲባል ማሳውን በቀበሌው ወይም በሌላ ቀበሌ ውስጥ ከሚገኝ ሌላ ባለይዞታ ማሳ ጋር መለዋወጥ ይችላል።
- በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ (1) ስር በተደነገገው መሰረት የሚደረግ የማሳዎች ልውውጥ ስምምነት ውል የሁለቱንም መሬቶች ፡
  - የለምነት ደረጃ፣
  - ስፋት፣
  - አዋሳኞች፣
  - የሚገኙበት ቀበሌ፣ ንኡስ ቀበሌ፣ ጎጥና ልዩ ስፍራ ማካተት ይኖርበታል።

የቀጠለ...

- በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1)ና (2) ስር የሰፈሩት ድንጋጌዎች በገጠር ቀበሌ ማዕከላት ውስጥ መኖሪያ ቤት መስራት የሚፈልጉ ባለይዞታዎች ቢኖሩ ማሳን በማሳ እንዳይለዋወጡ የመከልከል ውጤት አይኖራቸውም።
- ይዞታቸው ኩታ-ገጠም ይሆን ዘንድ በዚህ ደንብ መሰረት የማሳ ልውውጥ የሚያደርጉ የገጠር መሬት ባለይዞታዎች፡-
  - የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ በነፃ ይታደስላቸዋል፤
  - ከመሬት ልኬታ ጋር ተያያዥነት ያለውን ማናቸውንም አይነት አገልግሎት በነፃ ያገኛሉ።

የግጠር መሬት ይዞታ መብት ስለሚታጣባቸው ሁኔታዎች(አንቀጽ -11)

- በአዋጁ አንቀጽ 21 ንኡስ አንቀጽ (3) ስር በተደነገገው መሰረት በግብርና ስራ ሀብት ከፊጠረና በተጨማሪ ኢንቨስትመንት ላይ ተሰማርቶ ከሚገኝ ታታሪ አርሶ-አደር በስተቀር በክልሉ የገቢ ግብር ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት የደረጃ "ሀ"ና "ለ" ግብር ከፋይ ሆኖ የተገኘ ነጋዴ የይዞታ መሬቱን እንዲያጣ ይደረጋል፤ ዝርዝሩ ይህንን ደንብ ለማስፊጸም ወደፊት በሚወጣ መመሪያ ይደነገጋል።
- በአዋጁ አንቀጽ 21 ንኡስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ ቁጥር ለ. ስር የተደነገገው ቢኖርም የመጥፋት ዉሳኔ አሳዉጀው በህግ አግባብ መብታቸውን የሚጠይቁ ወራሾች በጊዜ ገደቡ ውስጥ በመሬቱ እየተጠቀሙ ከመቆየትና የጊዜ ገደቡ ሲያበቃ ደግሞ ይዞታውን ከመውረስ አይከለከሉም።

የቀጠለ...

- በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) ስር የተጠቀሰው ቢኖርም ይዞታውን በእጃቸው አድርገው በጊዜያዊነት የሚጠቀሙ ሰዎች ከሌሉ የክልሉ መንግሥት የጊዜ ገደቡ እስከሚደርስ ድረስ መሬቱን በጊዜያዊነት ይጠቀምበት ዘንድ ለሌላ ሰው ሊያከራየው ይችላል።

የገጠር መሬትን በግብርና ኢንቨስትመንት ለተሰማሩ የግል ባለሀብቶች በሊዝ ስለማስተላለፍ (አንቀጽ - 12)

- በማናቸውም አይነት የግብርና ኢንቨስትመንት ስራ ለመሰማራት የሚፈልጉ የግል ባለሃብቶች በጨረታ ተወዳድረው የገጠር መሬት ማግኘት ይችላሉ፡
- በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት ውድድሩ የሚካሄደው ከዚህ በታች የተመለከቱትን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል፡-
  - ምርቱን ወደ ሁለተኛ ደረጃ ምርት የመቀየርና ተጨማሪ ሃብት የመፍጠር አቅም፤
  - የታቀደው ፕሮጀክት ለአካባቢው ሕብረተ-ሰብ ይኖረዋል ተብሎ የሚገመተው ፋይዳ፤

የቀጠለ...

- የቀረበው የፕሮጀክት ሃሳብ ለተፈጥሮ ሀብት ልማትና ለአካባቢ ጥበቃ የሚኖረው አስተዋጽኦ፤
- የባለሃብቱ የማልማት አቅም፣ ዝግጁነት፣ ልምድና በዘርፉ የሚሳተፉ የሰለጠኑ ባለሙያዎችን ለመቅጠር በፕሮጀክት ሃሳቡ ውስጥ ያሳየው ፍላጎት፤
- በባንክ ስቴትመንት የተደገፈ የፋይናንስ አቅም፤
- በፕሮጀክቱ አማካኝነት የሚፈጠረው የስራ እድል ብዛትና ለሠራተኞች የሚያዘጋጀው ምቹ የሥራ አካባቢ።

የቀጠለ...

- ሰፋፊ የግብርና ኢንቨስትመንት በሚካሄድባቸው የክልሉ አካባቢዎች የብሎኪንግ አሰራር ስርዓት ተቀርጾ ተግባራዊ ይደረጋል። ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።
- በአዋጁ አንቀጽ 22 ንኡስ አንቀጽ (6) ስር በተደነገገው መሰረት ለግብርና ኢንቨስትመንት የተሰጠ ማናቸውም የግጠር መሬት የሊዝ ውል እንደገና ሊታደስ ይችላል፤
  - እድሳቱ የሚፈቀደው የተሻለ የልማት አፈፃፀም ላስመዘገቡ የግል ባለሃብቶች ነው።
  - ውሉ ሲታደስም በወቅቱ የሚኖረውን የመሬት ሊዝ ክፍያ ተመን ግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል። ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።

የቀጠለ...

- ለውድድር የቀረቡ የግብርና ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሚገመገሙበት፣ የውድድሩ ውጤት የሚገለጽበትና ይህንኑ አስመልክቶ ቅሬታ ቢኖር የሚቀርብበት ዝርዝር ሁኔታ ይህንን ደንብ ለማስፈጸም ወደፊት በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል።

ከግብርና ኢንቨስትመንት ውጭ የሚውል የገጠር መሬት በሊዝ ስለሚሰጥበት ሁኔታ (አንቀጽ -13)

- ከግብርና ኢንቨስትመንት ውጭ በገጠር መሬት ላይ ኢንቨስት ለማድረግ ጥያቄ የሚያቀርቡ የግል ባለሀብቶች በሚያቀርቡት የፕሮጀክት ሀሳብ ላይ ተመስርቶ ከዚህ በታች በተመለከቱት መስፈርቶች መሰረት በግልፅ ውድድር መሬት ሊሰጣቸው ይችላል፡-
  - በባንክ ስቴትመንት የተደገፈ የፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ጥቅል የኢንቨስትመንት ካፒታል መጠን፤
  - የታቀደው የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ገቢራዊ ቢደረግ የሚያመርተው ምርት ወይም የሚያበረክተው አገልግሎት ወይም ለውጭ ምንዛሪ የሚኖረው ጠቀሜታ፤

የቀጠለ...

- ፕሮጀክቱ የሚፈጥረው የሥራ ዕድል፤
- የቀረበው የፕሮጀክት ሃሳብ ለተፈጥሮ ሀብት ልማትና ለአካባቢ እንክብካቤ የሚኖረው አስተዋጽኦ፤
- ፕሮጀክቱ ከአካባቢው ህብረተ-ሰብ የሚረከበው ጥሬ ግብአትና በዚህም አማካኝነት ሊፈጠር የሚችለው የገበያ ትስስር።

➢ ለውድድር የቀረቡ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች፡

- የሚገመገሙበት፣
- የውድድሩ ውጤት የሚገለጽበትና
- ይህንኑ አስመልክቶ ቅሬታ ቢኖር የሚቀርብበት ዝርዝር ሁኔታ ይህንን ደንብ ለማስፈጸም ወደፊት በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል።

የግጠር መሬት ተጠቃሚ ግዴታዎች (አንቀጽ-14)

- ማንኛውም የገጠር መሬት ተጠቃሚ ይዞታው በውሃ ዳርቻዎችና በቦረቦር መሬቶች አካባቢ የሚገኝ ከሆነ የጥልቀቱን ሁለት እጥፍ ልክ ያለው የትኛውም የመሬቱ ክፍል ከእርሻ ስራ እንቅስቃሴ ነጻ ሆኖ መያዝ ይኖርበታል፤
- ሆኖም ይህንን ያልታረሰውን የውሃ ዳርቻና ቦረቦር መሬት በይዞታው ስር አድርጎ ለተለያዩ የጥምር ደንና ለእጸዋት ልማት ሊያውለው ይችላል።
- በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ስር የተደነገገው ቢኖርም ስልጣን በተሰጠው የመንግሥት አካል ህገወጥ ተብለው የተፈረጁትን ማንኛዎቹንም አይነት እጸዋት በየትኛውም አይነት ይዞታ ላይ ቢሆን ማብቀል ወይም ማልማት ህጋዊ የመሬት ይዞታን ተግድዶ እስከመልቀቅ የሚደርስ አስተዳደራዊ ቅጣት ሊያስከትል ይችላል።

የግጠር መሬት ይዞታን ለህዝብ አገልግሎት ስለማስለቀቅ (አንቀጽ -15)

- አግባብ ያለው የወረዳ አስተዳደር ጽህፈት ቤት የግጠርን መሬት ለህዝብ አገልግሎት ለማዋል አስፈላጊ ሆኖ ያገኘው እንደሆነ፡-

✓ ተገቢውን ካሳ በቅድሚያ በመክፈልና

✓ ተፈናቃዩ በዘላቂነት የሚቋቋምባቸውን የተለያዩ አማራጮች በማመቻቸት ከማንኛውም የመሬት ባለይዞታ ወይም ተጠቃሚ ለማስለቀቅ ይችላል።

- ሆኖም እርምጃው ተግባራዊ የሚደረገው ለባለመብቶች በቅድሚያ ተገቢው የቦታ አቅርቦት መሟላቱ ከተረጋገጠ በኋላ ይሆናል።

የቀጠለ...

- በየትኛውም ከተማ የፕላንና አስተዳደር ወሰን ክልል ውስጥ ለሚኖሩ ባለይዞታዎች ትክ የመኖሪያና የመስሪያ ቦታ ተለይቶ እንዲዘጋጅና ለተፈናቃዮች እንዲቀርብ ይደረጋል።
- ለተፈናቃዮች የሚሰጠውን የትክ ቦታ አቅርቦት አስመልክቶ መሟላት የሚገባቸው ዝርዝር መስፈርቶች በመመሪያ ይወሰናሉ።
- በከተማ የፕላን ወሰጥም ሆነ በገጠር ቀበሌ ማዕከላት ውስጥ በግል ይዞታቸው ላይ የመኖሪያ ቤት ወይም የንግድ ድርጅት የመገንባት ፍላጎታቸውን የገለጹ እንደሆነ ተቋቋሚዎች ቅድሚያ ይሰጣቸዋል።
- ዝርዝር አፈጻጸሙ በመመሪያ ይወሰናል።

የቀጠለ...

- ከከተማ አስተዳደር ውጭ በህዝብ ጥቅም አስገዳጂነት ከህጋዊ ይዞታቸው የሚነሱ የገጠር መሬት ባለይዞታዎች በህጉ መሰረት ፡-
  - አማራጭ የሰፈራ ቦታ፣
  - ትክ የእርሻና የግጦሽ መሬት እንዲያገኙ ይደረጋል። የልማት መሬት የሚጠይቁ አካላትም በመልሶ ማቋቋሙ ዕቅድ አተገባበር እንዲሳተፉ ሊጋበዙ ይችላሉ።
- በልማት ምክንያት ከመሬታቸው የሚፈናቀሉ ህጋዊ ባለይዞታዎች ይሸው መፈናቀል የሚያስከትልባቸው ጉዳት ከወዲሁ ታይቶ፡-
  - እንደየፍላጎታቸው በተናጠልም ሆነ በጋራ በመደራጀት በተለያዩ የስራ ዘርፎች ተፈላጊው ፕሮጀክት ተቀርጾላቸው ወደስራ እንዲገቡ ይደረጋል፤

የቀጠለ...

- በራሱ በክልሉ መንግሥትም ሆነ በአልሚ ባለሀብቶች አማካኝነት
  - የስራ እድል በቅድሚያ እንዲፈጠርላቸውና
  - ለስራ የደረሱ የቤተ-ሰብ አባሎቻቸውም በአካባቢው የሚካሄደው ልማት ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ተገቢው ክትትልና ድጋፍ ይደረግላቸዋል፤
- እንዳስፈላጊነቱ የብድር አገልግሎት ወይም ሌላ አይነት ልዩ ድጋፍ ይመቻችላቸዋል፤
- የሚያቀርቧቸው ምርቶች በገበያ ረገድ ተወዳዳሪዎች እንዲሆኑ በስልጠናና በግብይት እሴት ሰንሰለት ትስስር ፈጠራ ረገድ ተገቢው ድጋፍ ይደረግላቸዋል።

ስለገጠር መሬት አጠቃቀም እቅድ ዝግጅት፣ አተገባበርና ቁጥጥር

- መሪ የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድን ስለማዘጋጀትና ለዚሁ ስለሚያስፈልገው አደረጃጀት(አንቀጽ - 16)

- በዚህ ደንብ መሰረት፡-
  - ቀበሌን ወይም
  - ተፋሰስን መሰረት ያደረገና በማሳ ደረጃ ተፈጻሚ የሚሆን የገጠር መሬት አጠቃቀም እቅድ ይዘጋጃል፡
- ለዚህም ያመች ዘንድ የወረዳ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት የቀበሌ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ግብረ-ሀይልና አግባብ ያላቸውን አካላትም ሆነ ማህበረ-ሰቡን በማሳተፍ መሪ የመሬት አጠቃቀም እቅዱን የሚያዘጋጅ የቴክኒክ ኮሚቴ ያቋቁማል።

የግብረ-ሀይሉ አባላት ጥንቅር (አንቀጽ -17)

- የቀበሌ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ግብረ-ሀይል አባላት ከዚህ በታች የተመለከቱት ይሆናሉ፡-

- የቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ ሰብሳቢ፤
- የቀበሌው ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ባለሙያ ጸሀፊ፤
- የቀበሌው ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴዎች አባላት፤
- የቀበሌው ስራ አስኪያጅ አባል፤
- በቀበሌው ውስጥ የተመደበው የኮሚዩኒቲ ፖሊሲንግ ኦፊሰር አባል፤
- የቀበሌው አስተዳደርና ጸጥታ ዘርፍ ኃላፊ አባልና
- የቀበሌው ሚሊሻ ኮማንደር አባል።

የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት ጥንቅር (አንቀጽ-18)

- በቀበሌ ደረጃ የሚደራጅ አሳታፊ የገጠር መሬት አጠቃቀም እቅድ ዝግጅት ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት ከዚህ በታች የተመለከቱት ይሆናሉ፡-

- የቀበሌው ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ባለሙያ ሰብሳቢ፤
- የቀበሌው ግብርና ጽህፈት ቤት ኃላፊ ጸሀፊ፤
- የቀበሌው ስራ አስኪያጅ አባል፤
- በቀበሌው ነዋሪ ህብረተ-ሰብ የተመረጡና ከአምስት እስከ ሰባት የሚደርሱ ተወካዮች አባላት።

የግብረ-ሀይሉ ተግባርና ኃላፊነት (አንቀጽ-19)

- የቀበሌ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ግብረ-ሀይል በዚህ ደንብ መሰረት የሚከተሉት ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

- የቀበሌውን ህብረተሰብ በመሬት አጠቃቀም እቅድ ዝግጅት ተሳታፊ እንዲሆን ያስተባብራል፤
- የተዘጋጀውን የመሬት አጠቃቀም እቅድ በቀበሌው ምክር ቤት አቅርቦ ያጸድቃል፤
- በማሳ ደረጃ የመሬት አጠቃቀም እቅድ ትግበራን ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል ህግ ተጥሶ ሲገኝም ያስፈጽማል፤

የቀጠለ...

- ከተዘጋጀው የመሬት አጠቃቀም እቅድ ውጭ ያጠቃቀም ለውጥ አድርጎ በተገኘ በማንኛውም አካል ላይ የህግ ተጠያቂነት እንዲኖር ያደርጋል፤
- በአዋጁ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1ና 2 ስር ከተደነገገው የመሬት አጠቃቀምና አያያዝ ውጭ ሰርተው በሚገኙ አካላት ላይ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ይወስዳል።

የቴክኒክ ኮሚቴው ተግባርና ሃላፊነት (አንቀጽ-20)

- የቀበሌ አሳታፊ የገጠር መሬት አጠቃቀም መሪ እቅድ ዝግጅት ኮሚቴ

በዚህ ደንብ መሰረት የሚከተሉት ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

- ከወረዳው የመሬት አጠቃቀም ባለሙያዎች ቡድን ጋር በጋራ በመሆን የቀበሌዉን የመሬት አጠቃቀም እቅድ ያዘጋጃል፤
- የተዘጋጀውን የመሬት አጠቃቀም እቅድ ህብረተ-ሰቡ እንዲተቸውና የቀበሌው ምክር ቤት እንዲያፀድቀው ያስተባብራል፤
- ለቀበሌው ህብረተ-ሰብ ቀበሌን ወይም ተፋሰስን መሰረት አድርጎ ስለሚከናወን የመሬት አጠቃቀም እቅድ አዘገጃጀት ሂደትና ጠቀሜታ ተገቢውን ግንዛቤ ይፈጥራል፤
- በማሳ ደረጃ የተዘጋጀውን የመሬት አጠቃቀም እቅድ ለባለይዞታዎች በወቅቱ ያስረክባል፣ ተግባራዊነቱንም በቅርብ ይከታተላል።

የመሬት አጠቃቀም እቅድን ወቅታዊ ስለማድረግ(አንቀጽ-21)

- በአካባቢ ደረጃ የሚዘጋጅ አሳታፊ የገጠር መሬት አጠቃቀም እቅድ ጸንቶ የሚቆይበት ዘመን **አስር ዓመት** ይሆናል።
- በአዋጁ አንቀጽ 30 ንኡስ አንቀጽ (2) መሰረት ቀበሌን ወይም ተፋሰስን መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ የመሬት አጠቃቀም እቅድ ከዚህ በታች በተመለከቱት ምክንያቶች ሊከለስ ይችላል፡-
  - በየጊዜው በሚከሰቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ ለዉጦች ሳቢያ የተዘጋጀዉን እቅድ ገቢራዊ ማድረግ አስቸጋሪ ሆኖ ሲገኝ፤
  - በአፈጻጸም ሂደት ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ተካሂዶ በተገኘው ውጤት መሰረት የእቅዱን አተገባበር እድሜ ለማራዘም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ አለመኖሩ ከተረጋገጠ፤

ስለግጠር ቀበሌ ማዕከላት ምስረታና አስተዳደራቸው (አንቀጽ-22)

- በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የግጠር ቀበሌዎች የየራሳቸው አስተዳደራዊ ማዕከላት ይኖሯቸዋል።
  - እነዚህ አስተዳደራዊ ማእከላት የየቀበሌ አስተዳደሮቹ ዋና መቀመጫዎች በመሆን ጭምር ያገለግላሉ።
- በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጉዳዩ የሚመለከተው ወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት በጥናት ላይ ተመስርቶ በአንድ የግጠር ቀበሌ ውስጥ ከዋናው አስተዳደራዊ ማእከል ውጭ ሌሎች ተጨማሪ ማእከላት እንዲቋቋሙ ሊወስን ይችላል።
  - ሆኖም በአንድ የግጠር ቀበሌ ውስጥ ከአንድ በላይ የሆነ አስተዳደራዊ ማእከል ሊኖር አይችልም።

የቀጠለ...

- ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት በቋሚነት የቀበሌ ማእከላት ያልነበራቸው የገጠር ቀበሌዎች ያሉ እንደሆነ ወይም አዲስ የሚቋቋሙ ቀበሌዎች ሲኖሩ፣ በነዋሪው ህብረተ-ሰብ ተሳታፊነትና ጉዳዩ በሚመለከተው ቀበሌ ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ ሰጭነት ማእከሉ የሚመሰረትበት ቦታ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡-
  - የመሬቱ ለምነት ደረጃ በንጽጽር ዝቅተኛ የሆነ፤
  - ተዳፋትነቱ ለግንባታ ምቹ የሆነ፤
  - በቂ የዉሃ አቅርቦት ያለው ወይም ቢፈለግ በቀላሉ ሊገኝበት የሚችል፤
  - ለመሬት መንሸራተትና ለሌሎች መሰል አደጋዎች ተጋላጭ ያልሆነና የደህንነት ስጋት የሌለበት፤
  - በተቻለ መጠን የመሰረተ-ልማት አውታሮችና የአገልግሎት ተቋማት የተገነቡበት ወይም እነዚህኑ ለመገንባት አመቺ የሆነ።

የቀጠለ...

- በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ፊደል ተራ ቁጥር ሀ.ና “ለ. ስር የሰፈሩት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው አብዛኛው የቀበሌው ነዋሪ ህዝብ ያማክለኛል ብሎ ያመነበትና ምክር ቤቱ ተወያይቶ ያጸደቀው ቦታ በማዕከልነት ይመረጣል።
- ለገጠር ቀበሌ ማዕከላት ምስረታ በሚውል በማናቸውም መሬት ላይ ህጋዊ ይዞታ ያላቸው ባለይዞታዎች ስፍራውን እንዲለቅቁ ከመገደዳቸው በፊት ተገቢዉን ካሳ ወይም ትክ መሬት በቅድሚያ ማግኘት አለባቸው።
- በገጠር ቀበሌ ማእከላት ውስጥ ከመሬት ሽንሸና፣ አሰጣጥና የመረጃ አስተዳደር ጋር ተያያዥነት ያላቸው ማናቸዉም ቴክኒካዊና አስተዳደራዊ ተግባራት አግባብ ባላቸው የወረዳና የቀበሌ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤቶች አማካኝነት ይከናወናሉ፤ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።

በማእከላቱ ውስጥ ስለሚከናወን የመሬት አሰጣጥና አጠቃቀም ሁኔታዎች (አንቀጽ-23)

- ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟላ ማንኛውም ሰው በገጠር ቀበሌ ማዕከላት ውስጥ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ማግኘት ይችላል፡-

- እድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ፤
- በቀበሌው ውስጥ ቢያንስ ለሁለት ተከታታይ ዓመታት የኖረና
  - ✓ በግብርና፤
  - ✓ በንግድ ወይም
  - ✓ በሌላ በማናቸውም መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ባልሆነ ድርጅት አማካኝነት ተቀጥሮ የሚሰራ፤
- የታቀደውን ግንባታ በገባው ውል መሰረት በ18 ወራት ውስጥ የማጠናቀቅ አቅም ያለው፤

የቀጠለ...

- መሬቱን በትክ ቦታ ለመለወጥ የሚችል ወይም ለተፈናቃዩ ተገቢውን ካሳ በቅድሚያ የመክፈል አቅም ያለው፤
- የግንባታ ፕሮጀክቱን በተሰጠው ፕላን መሰረት ለማከናወን የሚችል።

➢ በአዋጁ አንቀጽ 31 ንኡስ አንቀጽ (6) ስር በተደነገገው መሰረት ፡

- ወላጆቻቸውን በሞት ያጡ ህፃናት፣
- አካል ጉዳተኞች፣
- አቅመ-ደካሞች፣
- ሴቶችና
- አረጋዉያን የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ እንዲያገኙ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ከዚህ በላይ በንኡስ አንቀጽ (1) ከፊደል ተራ ቁጥር ሀ. እስከተራ ቁጥር ሠ. ድረስ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች አሟልተው ሲገኙ ይሆናል።

✓ ሆኖም እድሜን የተመለከተው መስፈርት ወላጆቻቸዉን በሞት ባጡ ህፃናት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

- በልውውጥ ወይም ካሳ በመክፈል የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ የሚሰጣቸው አካላት የሚያገኙት መሬት ስፋት ቀበሌው በሚኖረው የመሬት አቅርቦት አቅም የሚወሰን ሆኖ ለአንድ የቤተሰብ ኃላፊ ከ200 እስከ 500 ካሬ ሜትር የግንባታ ቦታ ሊሆን ይችላል።
- በቀበሌው ውስጥ የሚኖር ማንኛውም አርሶ-አደር ከዚህ በላይ በንኡስ አንቀጽ (1) ስር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች አሟልቶ እስከተገኘ ድረስ ከማዕከሉ ውጭ ሌላ ቤትና ቦታ ቢኖረው እንኳ በማዕከሉ ውስጥ የቤት መስሪያ ቦታ ከማግኘት አይታገድም።

የቀጠለ...

- ማንኛውም ሰው በአንድ የገጠር ቀበሌ ማእከል ውስጥ አንድ የምሪት ቦታ ብቻ ይኖረዋል፤
- ሆኖም ቀደም ሲል ከአንድ በላይ የሆኑ ቤቶች ያላቸውን ነባር ባለይዞታዎች በተመለከተ እያንዳንዱ ከ500 ካሬ ሜትር ስፋት እስካልበለጠ ድረስ እየታየ እንዲጸድቅላቸው ይደረጋል።
- ለገጠር ቀበሌ ማዕከል ግንባታ ሲባል የይዞታ መሬት የሚወሰድባቸው አርሶ-አደሮች የተገኙ እንደሆነ እያንዳንዱ የቤተ-ሰብ ሃላፊ ከሚለቀው አጠቃላይ መሬት ላይ ቅድሚያ እየተሰጠው እስከ 500 (500 ካሬ ሜትር የሚደርስ ቦታ የማግኘት መብቱ ይከበርለታል።

የቀጠለ...

- በቤት ውስጥ አብረው የሚኖሩና እድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆናቸው ልጆችና በአዋጁ ውስጥ ቤተ-ሰብ ተብሎ በተተረጎመው ሀረግ የሚሸፈኑ ወገኖች በግብርና ስራ የተሰማሩና በዚያው አካባቢ ቋሚ አድራሻ ያላቸው መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ የባለይዞታው መሬት በቂ ሆኖ እስከተገኘ ድረስ በማእከሉ የቦታ ሽንሸና ዝቅተኛውን የቦታ ምሪት መጠን ለእያንዳንዳቸው አንድ የምሪት ቦታ ሊሰጥ ይችላል። ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።
- በቀበሌው ውስጥ ስራቸውን የሚያካሂዱ የተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለዚሁ ተግባር የሚሰጣቸው የመሬት ይዞታ ስፋት ይህንን ደንብ ተከትሎ ወደፊት በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል።

የቀጠለ...

- ነባር ተቋማት ስራቸውን የሚያከናውኑበት በቂ ስፍራ እንደሌላቸው ግልጸው ያመለከቱ እንደሆነ ከአካባቢው ለሚነሱ ባለይዞታዎች በቅድሚያ ትክ እየተሰጠ ወይም ተገቢው ካሳ እየተከፈለ ተጨማሪ የማስፋፊያ ቦታ እንዲያገኙ ሊደረግ ይችላል። ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።
- በማእከሉ ውስጥ ለሚካሄዱ የንግድ እንቅስቃሴዎች የሚጠየቀው ቦታ ነጋዴዎች በሚያቀርቡት የፕሮጀክት ሃሳብና ቀበሌው ለልማት ተነሺዎች በሚኖረው ካሳ የመክፈል አቅም ላይ ተመስርቶ ፡
  - በውድድርና
  - እንዳስፈላጊነቱ በምደባ ይሰጣል።
  - ሆኖም ምደባው የሚከናወነው አግባብ ባለው የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት የውሳኔ አስተያየት መነሻነት የዞኑ አስተዳደር ምክር ቤት ሲፈቅድ ብቻ ይሆናል።

የቀጠለ...

- አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ለገጠር ቀበሌ ማእከልነት በተመረጡ ስፍራዎች ውስጥ የተገነቡና በሽንሽና ፕላኑ መሰረት መስፈርቱን የሚያሟሉ የትኛዎቹም ቤቶች ባሉበት ሁኔታ እውቅና ተሰጥቷቸው ይቀጥላሉ።
- ሆኖም የሽንሽና ፕላኑ ሲሰራ ከፕላኑ ውጭ ተሰርተው የሚገኙትን ቤቶች በተመለከተ ፈርሰውና ትክ ቦታ ተዘጋጅቶላቸው በፕላኑ መሰረት እንደገና መገንባት ይኖርባቸዋል።
- በገጠር ቀበሌ ማእከላት ውስጥ የተገነቡ መኖሪያ ቤቶች የዲዛይንና የግንባታ ጥራት መስፈርቶችን አሟልተው ስለመገኘታቸው አግባብ ባለው የወረዳ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት ተረጋግጦ ፡
- ሊሸጡ፣
- የእዳ ዋስትና ሆነው ሊያዙም ሆነ
- በማናቸውም መንገድ ለሶስተኛ ወገን ሊተላለፉ ይችላሉ። ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።

የቀጠለ...

- የስመ-ንብረት ዝውውሩም ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በመፈጸም ማዕከሉ በሚገኝበት ወረዳ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት በኩል ይከናወናል። ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል
- በማእከላት ውስጥም ሆነ ከማእከላት ውጭ ለግብርናም ሆነ ከግብርና ውጭ ለሆነ አላማ በገጠር መሬት ላይ የሚካሄዱ የኢንቬስትሜንት ፕሮጀክቶችን በተመለከተ፡

- ዲዛይን የማጽደቁ፣
- የግንባታ ፈቃድ የመስጠቱ፣
- ስመ-ንብረት የማዛወሩና የመቆጣጠሩ ስልጣን አግባብ ያላቸው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ተቋማት ይሆናል። ዝርዝሩ በመመሪያ ይደነገጋል።

❖ ይዞታን ስለመለካት (አንቀጽ -24)

- ማናቸውም የግጠር መሬት በሚለካበት ጊዜ የመሬቱ አዋሳኝ ባለይዞታዎች ወይም ተጠቃሚዎች ጥሪ ተደርጎላቸው በስፍራው እንዲገኙና ድንበራቸውን በስምምነት ለይተው በማሳየት ይዞታቸውን እንዲያስመዘግቡ ይደረጋል።
- በጥሪው መሰረት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለይዞታዎች ካልተገኙ የንኡስ ቀበሌው መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ ስለመሬቱ መረጃው ባላቸው ታዋቂ የአካባቢው ነዋሪዎች እማኝነት ታግዞ ልኬታውን ያካሂዳል።

የቀጠለ...

- በመሬቱ አለካክና በድንበሩ አከላለል ረገድ ቅሬታ የተሰማው ማንኛውም ባለይዞታ መረጃው ለነዋሪው ህበረተ-ሰብ ቀርቦ ከተተቸበት ዕለት ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ጉዳዩ እንደገና ይታይለት ዘንድ በየደረጃው ለሚገኘው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አካል አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው።

የግል የመሬት ቅየሳ ድርጅቶችን ስለማሳተፍ (አንቀጽ-25)

- በአዋጁ አንቀጽ 33 ንኡስ አንቀጽ (7) ስር በተደነገገው መሰረት ከዚህ በታች የተመለከቱትን መስፈርቶች አሟልተው እስከተገኙ ድረስ ህጋዊ ፈቃድ ያላቸው የግል የቅየሳ ድርጅቶች በመሬት ቅየሳና ልኬታ ስራው ላይ ሊሳተፉ ይችላሉ፡-

- ዘርፉ የሚጠይቃቸውን ዘመናዊ የቅየሳ መሳሪያዎችና ሌሎች አስፈላጊ ቁሳቁሶች ማሟላታቸው ሲረጋገጥ፤
- በሙያው የሰለጠኑና ልምድ ያላቸውን ባለሙያዎች ያካተቱ ሆነው ሲገኙ፤
- የታደሰ የሙያ ፈቃድ ያላቸውና የዘመኑን ግብር የከፈሉ መሆናቸው ሲረጋገጥ።

ስለ ግጠር መሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር(አንቀጽ-26)

- የግጠር መሬት በይዞታ የተሰጠው ማንኛውም ሰው የመሬቱ ዝርዝር የተመዘገበበት የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በስሙ ተዘጋጅቶና ፎቶግራፉ ተለጥፎበት አግባብ ባለው የወረዳ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት አማካኝነት ይሰጠዋል።
- የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ በማናቸውም ሁኔታ የጠፋበት፣ የተቀደደበት ወይም የተበላሸበት ማንኛውም ሰው ይኸው እንደታወቀ፡-
  - አግባብ ላለው የወረዳ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት አመልክቶና
  - ስለዚሁ ከፖሊስ ወይም
  - ከማህበራዊ ፍርድ ቤት የተሰጠ ማስረጃ አቅርቦ ወደፊት በመመሪያ የሚወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ በመፈጸም እንደገና ማውጣት ይችላል።

የቀጠለ...

- የግጠር መሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ባህረ-መዝገብና የኤሌክትሮኒክስ ቅጂው ያዘጋጁ ባለሙያ ሙሉ ስምና ፊርማ ካረፈባቸው በኋላ በጽህፈት ቤቱ ሃላፊ ወይም በተወካዩ ፊርማና ማህተም መረጋገጥ አለባቸው።
- ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት ያልተፈረመባቸው ደብተሮችና ባህረ-መዝገቦች በመረጃ ማጥራት ሂደቱ የሚለዩበትን ቃለ-ጉባኤ መሰረት በማድረግ ያዘጋጀው ባለሙያ ስምና ፊርማ ካረፈባቸው በኋላ በጽህፈት ቤቱ ሃላፊ ወይም በተወካዩ ፊርማና ማህተም እንደገና እየተረጋገጡ ይቀመጣሉ።

የቀጠለ...

- በህግ ከተወሰነው የአንድ ማሳ ዝቅተኛ መጠን በታች የሆነ የትኛውም የግጠር መሬት በይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ውስጥ ለብቻው አይመዘገብም፤
  - ሆኖም ይህ ድንጋጌ አዋጁ ተሻሽሎ ከመውጣቱ በፊት ለነበሩት አነስተኛ ይዞታዎች ማረጋገጫ ደብተር ከመስጠት አያግድም፡
- በዚህ አዋጅ መሰረት ተፈላጊውን የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ሳያወጣ በገጠር መሬት ሲጠቀም የተገኘ ማንኛውም ሰው በሚከተለው አኳኋን ከቃል ማስጠንቀቂያ ጀምሮ መሬቱን ተገድዶ እስከመልቀቅ የሚደርስ እርምጃ ሊወሰድበት ይችላል፡-
  - መጀመሪያ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ደብተሩን እንዲያወጣ በቀበሌው ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት በኩል የቃል ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤

የቀጠለ...

- በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ደብተሩን ሳያወጣ የቀረ እንደሆነ በወረዳው ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት አማካኝነት የሶስት ወር የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤
- በጽሁፍ ማስጠንቀቂያው መሰረት ደብተሩን ያላወጣ እንደሆነ ለአንድ አመት ያህል በይዞታው የመጠቀም መብቱን እንዲያጣና መሬቱ ለሌላ ሰው ተከራይቶ አገልግሎት እየሰጠ እንዲቆይ በቀበሌው መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት ይወሰንበታል፤
- በተጠቀሰው የአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ደብተሩን ካላወጣ ደግሞ የመሬት ይዞታው ተነጥቆ ወደመሬት ባንክ እንዲገባ ይደረጋል።

የቀጠለ...

- የወል መሬት ባለይዞታዎች የዚሁ መሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በተጠቃሚዎች ስም ተዘጋጅቶ የሚሰጣቸው። ሲሆን እስከተቻለ ድረስም የመሬቱ ተጠቃሚዎች ስም ዝርዝር እንዲያያዝ ተደርጎና የይዞታው ልዩ መጠሪያ ተጠቅሶ ራሳቸው በሚመርጡት ወኪል ሃላፊነት እንዲያዝና እንዲጠበቅ ይደረጋል፤
- በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር የተደነገገው ቢኖርም በወልና በድርጅቶች ስም በሚሰጥ የግጠር መሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ላይ **የባለይዞታዎችን ፎቶግራፍ መለጠፍ አስፈላጊ አይሆንም**።
- የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በዚህ ደንብ መሰረት የሚጠይቁት የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በተቋማት ስም ተዘጋጅቶ ይሰጣቸዋል።

በገጠር መሬት ይዞታ ማረጋገጫ መረጃ ሰነዶች ላይ ተቃውሞ ስለሚቀርብበትና ማሻሻያ ስለሚደረግበት ሁኔታ (አንቀጽ-27)

- በምዝገባ ሂደት ተረጋግጦ የተያዘ የገጠር መሬት መረጃ የመጨረሻ ሆኖ በገጠር መሬት መዝገብ ውስጥ ከመግባቱ በፊት ቅሬታ አለኝ የሚል ማንኛውም ባለይዞታ መረጃው በተመዘገበ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አቤቱታውን ለመዝጋቢው አካል በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል።
- በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት አቤቱታ የቀረበለት አካል አቤቱታው በቀረበ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ምላሹን በጽሁፍ የመስጠት ግዴታ አለበት።

የቀጠለ...

- አቤቱታው የቀረበለት አካል በወቅቱ ምላሽ ያልሰጠው ወይም የሰጠው ምላሽ ያላረካው እንደሆነ አቤቱታ አቅራቢው ይግባኙን ቀጥሎ ላለው የተቋሙ እርከን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል።
- ይግባኙ የቀረበለት የበላይ አካልም ይግባኙ በቀረበለት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በጽሁፍ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል።
- በዚህ አካል ምላሽ ያልተሰጠው ወይም በተሰጠው ምላሽ ያልተስማማ ማንኛውም ወገን አቤቱታዉን በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ለመደበኛ ፍርድቤት ሊያቀርብ ይችላል።

የቀጠለ...

- በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር የተደነገገው የጊዜ ገደብ ካለፉ በኋላ ስለተመዘገበው መረጃ የሚቀርብ ማናቸውም አይነት ተቃውሞ ተቀባይነት አይኖረውም።
- ሆኖም ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት አጋጥሞት በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቅሬታውን ለማቅረብ ያልቻለ ማንኛውም ባለይዞታ ቅሬታውን በወቅቱ ያላቀረበበትን ምክንያት ስልጣን ካለው አካል በተሰጠ የፅሁፍ ማስረጃ አስደግፎ ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ በተለየ ሁኔታ ሊስተናገድ ይችላል።
- በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (5) መሰረት ዘግይቶ የሚቀርብ ቅሬታ ከአቅም በላይ የሆነው ምክንያት በተወገደ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መቅረብ ያለበት ሆኖ የቅሬታ አቀራረብና ምላሽ አሰጣጡ ሂደት በንኡስ አንቀጽ (3)ና (4) ድንጋጌዎች ስር የተቀመጠውን ስርአት የተከተለ ይሆናል።

የቀጠለ...

- በዚህ አንቀጽ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ድንጋጌዎች ቢኖሩም ፡-
  - ህጻናትን፣
  - አካል ጉዳተኞችን፣
  - አቅመ-ደካሞችንና
  - አረጋውያንን የሚመለከት የገጠር መሬት ባለይዞታነት መረጃ በምዝገባ ሂደት ከተጣራ በኋላ የመጨረሻ ሆኖ በገጠር መሬት መዝገብ ውስጥ ከመግባቱ በፊት እነዚሁ ወገኖች ቅሬታ አለን የሚሉ ከሆነ አቤቱታቸውን በ60 ቀናት ጊዜ ውስጥ ማቅረብ ይችላሉ።

የይዞታና የማሳ መለያ ቁጥር አሰጣጥን ስለመወሰን (አንቀጽ- 28)

- በዚህ ደንብ መሰረት የይዞታና የማሳ መለያ ቁጥር የሚሰጠው የክልል መንግሥቱን አስተዳደራዊ እርከኖች መሰረት በማድረግ ከላይ ወደታች ይሆናል።
- ከዚህ በላይ በንኡስ አንቀጽ (1) ስር በተደነገገው መሰረት የክልል፣ የዞን፣ የወረዳ፣ የቀበሌ፣ የይዞታና የማሳ ልዩ መለያ ኮድ እየተሰጠ የሚመዘገብ ሲሆን፡-
  - የክልልና የዞን መለያ ኮድ አሰጣጥ በእንግሊዝኛ ቋንቋ አልፋ ቤት ይሆናል፤
  - ለእያንዳንዱ ወረዳ፣ ቀበሌ፣ ባለይዞታና ማሳ መለያ ኮድ የሚሰጠው በቁጥር ይሆናል።

የቀጠለ...

- የክልል፣ የዞን፣ የወረዳና የቀበሌ መለያ ኮዶች የሚሰጡት በቢሮው ነው።
- የባለይዞታና የማሳ መለያ ኮዶች የሚሰጡት በወረዳና በቀበሌ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አካላት ይሆናል።

ስለመሬት መረጃ ምዝገባና ወቅታዊ አደራረግ(አንቀጽ-29)

- የግጠር መሬት ይዞታ ምዝገባ መረጃ እንዲሻሻል፣ ወቅታዊ እንዲደረግ ወይም ይዞታው እንዲተላለፍለት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ማስረጃውን በማያያዝ ጥያቄውን በጽሁፍ አግባብ ላለው ቀበሌ ወይም ወረዳ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት ማቅረብ ይችላል።
- ማመልከቻው የቀረበለት የወረዳ ገጠር አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት ከሆነ ጥያቄው በቀረበለት በ15 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለቀበሌው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት ያሳዉቃል።

የቀጠለ...

- በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት የግጠር መሬት ይዞታ ምዝገባ መረጃ፡-
  - እንዲሻሻል፣
  - ወቅታዊ እንዲደረግ ወይም
  - ይዞታ ወደሌላ ሰው እንዲተላለፍ ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ ተቃዋሚ ወይም መብት አለኝ የሚል ወገን ቢኖር እይቀርብ ዘንድ ይህንኑ የሚገልጽ ማስታወቂያ በቀበሌው አስተዳደር ጽህፈት ቤት፣ በቀበሌው ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት፣ እንዲሁም አመቺ ነው ተብሎ በሚገመት በሌላ በማናቸውም ስፍራ ለ15 ተከታታይ ቀናት መለጠፍ አለበት፡

የቀጠለ...

- የቀበሌው ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት የማስታወቂያ ጊዜው በተጠናቀቀ በ15 ቀናት ውስጥ መረጃውን አጣርቶ ለወረዳው ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት ይልካል።
- የወረዳው ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤትም በቀበሌ ደረጃ የተጣራው ጉዳይ በደረሰው በ15 ቀን ውስጥ የመረጃውን ትክክለኛነት አረጋግጦ ወቅታዊ በማድረግ ለጠየቀው ወገን መስጠት ይኖርበታል።
- የባለይዞታም ሆነ የማሳ ወይም የሁለቱም ለዉጥ በሚኖርበት ጊዜ የመሬት ምዝገባ ሰነዱን ወቅታዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉት ዝርዝር ሁኔታዎች በመመሪያ ይወሰናሉ።

ስለአገልግሎት ክፍያዎች (አንቀጽ -30)

በአዋጁ አንቀጽ 42 ንኡስ አንቀጽ (2)ና (3) ስር በተደነገገው መሰረት የገጠር መሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ከተሰጠ በኋላ፡

- የኪራይ ውል እንዲመዘገብ ወይም
- እንዲታደስ፣
- ይዞታውም ሆነ የመጠቀም መብቱ እንደሁኔታው በውርስ፣ በስጦታ ወይም በልውውጥ ለሌላ ሰው እንዲተላለፍ ወይም
- ደብተሩ በሚጠፋበት ወይም በሚበላሽበት ወቅት በአዲስ እንዲተካ በባለመብቱ በኩል ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ ተገቢው የአገልግሎት ክፍያ ይፈጸማል።

የቀጠለ...

- በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት ለሚሰጡት የተለያዩ አገልግሎቶች የሚጠየቀው ክፍያ መጠን የሚወሰነው እያንዳንዱ አገልግሎት የሚጠይቀውን ወጪና ጊዜ ግምት ውስጥ በማስገባት ሲሆን ዝቅተኛው ክፍያ ሃምሳ ብር ሆኖ ከፍተኛው ደግሞ አንድ መቶ ሃምሳ ብር ይሆናል። ዝርዝሩ በመመሪያ ይደነገጋል፡
- በገጠር ኢንቨስትመንት የሚሰማራ ማንኛውም ባለሀብት ፡
  - ለዚሁ የሚገባውን የሊዝ ውል ሲያስመዘግብ ሁለት መቶ ብር፣
  - ይኸው በሚታደስበት ጊዜ ደግሞ አንድ ሽህ ብር በሄክታር የአገልግሎት ክፍያ ይፈጽማል።
- ከግብርና ውጭ የሆኑና በገጠር መሬት ላይ የሚካሄዱ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የመሬት ሊዝ ዋጋም ሆነ የአገልግሎት ክፍያ አፈጻጸም በገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ተቋም ይከናወናል። ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።

ስለገጠር መሬት ካዳስተር ቅየሳ አገልግሎት(አንቀጽ-31)

- በገጠር መሬት ካዳስተር ቅየሳ ወቅት በስራ ላይ የሚውለው የርዝመት መለኪያ አሀድ ሜትር ሲሆን የስፋቱ መለኪያ ደግሞ ሄክታር ይሆናል።
- የወረዳና የቀበሌ መሰረታዊ ካርታዎች፣ እንዲሁም የባለይዞታዎች የማሳ ካርታዎች ሊይዟቸው የሚገቡ ዝርዝር መረጃዎች በመመሪያ ይወሰናሉ።
- ሁለተኛ ደረጃ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ለማዘጋጀት መከናወን ያለባቸው ዝርዝር ተግባራት ተለይተው በመመሪያ ይወሰናሉ።

የካዳስተር መረጃዎችን ወቅታዊ ስለማድረግ(አንቀጽ -32)

- የባለይዞታና የማሳ ለውጥ በሚደረግበት ጊዜ ሁሉ የካዳስተር ቅየሳው መረጃ ወቅታዊ መደረግ አለበት፡
- መሬትና መሬት-ነክ ሀብቶችን የሚመለከቱ መብቶችንና ግዴታዎችን የያዙ ሰነዶችና ሌሎች መረጃዎች ምን ጊዜም ቢሆን ለህዝብ ክፍትና ተደራሽ መሆን ይኖርባቸዋል።
- የእነዚህን መረጃዎች ቅጅ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው አስፈላጊውን የአገልግሎት ክፍያ ፈጽሞ ሊወስድ ይችላል። የአገልግሎት ክፍያው ተመን በመመሪያ ይወሰናል።

ስለደንቡ አስፈጻሚ አካላት

- **ለኢንቨስትመንት ሊውል ስለሚችል መሬት አሰጣጥ (አንቀጽ - 33)**

- የዞን ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መምሪያ በተደራጀበት ዞን ውስጥ የሚቀርቡትን የኢንቨስትመንት መሬት ጥያቄዎች አስመልክቶ በአዋጁና በዚህ ደንብ በተዘረዘሩት መስፈርቶች መሰረት የፕሮጀክት ሀሳብ መግለጫዎችን አወዳድሮ ከአሸናፊው ጋር ውል በመያዝ ስፋቱ እስከ 10 ሄክታር የሚደርስ መሬት የመስጠትና ይህንኑ የማስተዳደር ስልጣን አለው።

የቀጠለ...

- በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ስር የተደነገገው ቢኖርም የመምሪያውን አፈጻጸም ለማቀላጠፍ ወይም ለማቃናት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ቢሮው ተገቢውን በቅርብ ሊከታተልና በቴክኒክ ረገድ እገዛ ሊያደርግ ይችላል።
- ከ10 ሄክታር በላይ የሆነን የኢንቨስትመንት መሬት በተመለከተ ውሉ የሚያዘውና አስተዳደሩ የሚመራው በቢሮው አማካኝነት ሲሆን አግባብ ያላቸው የዞን ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መምሪያዎች፡-
  - መሬቱን በመለየት፣
  - በመከታተልና በመደገፍ ረገድ አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋሉ።

ስለንኡስ ቀበሌ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴዎች ተግባርና ሃላፊነት (አንቀጽ- 34)

- በአዋጁ ውስጥ ከአንቀጽ 46 እስከአንቀጽ 50 ድረስ የሰፈሩት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የንዑስ ቀበሌ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴዎች ይህንን ደንብ በማስፈፀም ረገድ የሚከተሉት ዝርዝር ተግባርና ሀላፊነቶች ይኖሯቸዋል፡-
  - የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጉዳዮችን አስመልክቶ የንዑስ ቀበሌውን ነዋሪ ህብረተ-ሰብ ይወክላሉ፤
  - ህብረተ-ሰቡ በመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጉዳዮች ረገድ ተገቢውን ግንዛቤ እንዲይዝ ያደርጋሉ፤

የቀጠለ...

- በንዑስ ቀበሌው ውስጥ የሚገኙትን የመሬት ተጠቃሚዎች ዝርዝር መዝግበው ይይዛሉ፣ ይጠብቃሉ፣ ይህንኑ ለታቀፉበት ቀበሌ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አቢይ ኮሚቴ በወቅቱ ያስተላልፋሉ፤
- አዳዲስ የመሬት ይዞታ ጥያቄዎችን ያሰባስባሉ፣ ከንዑስ ቀበሌው ነዋሪ ህብረተ-ሰብ ጋር በመመካከር ቅደም-ተከተል እያስያዙ ለቀበሌው ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አቢይ ኮሚቴ ያቀርባሉ፤
- ግዴታቸዉን ለማይወጡት የመሬት ባለይዞታዎችና ተጠቃሚዎች ምክርና ተግሳጽ ይሰጣሉ፣ ይህንኑ ተግባራዊ ሳያደርጉ በቀሩት ላይ ደግሞ ለቀበሌው ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አቢይ ኮሚቴ ሪፖርት ያደርጋሉ።

በቀድሞ ህጎች ስለተገኙ መብቶችና ግዴታዎች (አንቀጽ- 35)

- ይህ ደንብ ከመጽናቱ በፊት ሲሰራባቸው በቆዩት ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች የተገኙ መብቶችና የተጣሉ ግዴታዎች የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች በግልጽ እስካልተቃረኑ ድረስ የጸኑ ሆነው ይቀጥላሉ።

ስለተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች (አንቀጽ-37)

- በስራ ላይ ያለው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ስርአት ማስፈጸሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 51/1999 ዓ.ም ተሽሮ በዚህ ደንብ ተተክቷል።
- ይህንን ደንብ የሚቃረን ማናቸውም ሌላ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ ደንብ ውስጥ የተሸፈኑትን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ (አንቀጽ-39)

- ይህ ደንብ በክልሉ መንግሥት ዝክረ-ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አመሰግናለሁ